# ስደተኛው አምባገነን መንግስት  ከ እሸቴ ውለታው።

አምባገነን መንግሥትን በሁለገብ ትግል አስወግጀ ሁሉም ዜጎች እኩል የሆኑባት የዲሞክራሲ አስተዳደርና ሥርዐት እገነባለሁ ብሎ የሚታገልና በህዝቦች ተስፋ የተጣለበት ድርጅት እንዴት የሰዎችን የመናገር ፣የመፃፍ፣የመደራጀት፣ የመተቸትና  የመሰብሰብ መብት ና ነጻነት ለመግፈፍና ለመደፍጠጥ እንዳቅሜቴ ሲሞክርና ሲንቀሳቀስ ማየት በጣም ያሳዝናል ።

ግንቦት ሰባት ከኢትዮጵያ ስትራቲጅክ ጠላት ተብሎ ከሚታመን ሀገራችን አሁን ላለችበት ሁለተናዊ ቀውስ ና ፈተና ዋነኛ የፊት መሪና ተዋናይ ከነበረው ከሻቢያና ከኢሳያስ አፈወርቅ ጋር የጠበቀ የቃል ኪዳን ትስስር ብሎ ድርጅቱ ከፍተኛ ተፅእኖ በሚደርግበት  በእሳት ራዲዩና ቴሌብጅን ሲስነግር ና ፕሮግራም በማሰራት ስለ ፕሪዘርዳንቱ  ሩቅ አሳቤነት አገራችንም የኒህ ቸርና አስተዋይ መሪ አካል ትሆን ዘንድ ይህን ያህል ተሰርቶል በሚል የቀረበው ዝግጅት ህዝባዊ ውይይት፤ ክርክርና ነቀፌታ አያጋጥመኝም በሚል እምነት በማሰብና በመወሰን  እሳት ላይ የተዘገበውን ህዝቡ አሜን ብሎ ይቀበለዋልና ያምናል በሚል ስሌት አስቦ ከሆነ በድርጅቱ በጣም አዝናለሁ። ማዘን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ህዝብ እውቀትና ግንዛቤ ዝቅ አድርጎ በንቀት በማየቱ አፍሪበታለሁ ። ኢትዮጵውያን ከኤርትራ በተለይ ከኢሳያስ አፈወርቂ ጋር ስለሚኖረን ግንኙነት እንደህዝብ ና እንደ ሀገር በጣም ያገባናል ምክንያቱም በታሪክ ሻቢያና ኢሳያስ ለሀገራችን መልካም አይመኙም ከሚል አስተሳሰብ የመነጨ ነዉ። ይህ ደግሞ ታሪካዊ ሀቅ ነው።

ጋዜጠኛ አበበ በለው ይህን ስለ ሻቢያና ኢሳያስ አፈወርቂ በጣም ገዝፎና አምሮ በእሳት የቀረበን ዘገባ ማወያየትና ህዝቡን ማነጋገር ስለ ነበረበት ተምክሮ ያላቸውን ስወች በማነጋገሩና በዳላስ ስብሰባ ኤርትራን በተመለከተ ባደረገው ንግግር  በስደተኛው አምባገነን መንግሥት በግንቦት ሰባት ጦርነት ከተከፈተበት ሦስት ሳምንት ሆነው እንደ ገልፍ ጦርነት ለምን?  አምባገነን የህዋት ኢህአደግን መንግስትን ለመጣል ሙሉ ወታደራዊ ዝግጅትና ድርጅት አለኝ. በቅርቡ ለምጀምረው ወታደራዊ ኦፐሬሽን የኢትዮጵያ ህዝብ ና የወያኔ ጦር ከነፃ አውጭው ሠራዊት ጋር ይቀላቀል ብሎ ጥሪ እያደረገ ያለ ድርጅት  ከአፍሪካ ግዙፍ ጦር አለኝ ከሚለው መንግሥት ጋር ለመግጠም ከነ ሙሉ ዝግጅቱ ያለ  ኃይል ግንቦት ሰባት ለምን በአንድ በሎካል ደረጃ ያውም በውጭ ሀገር  በሚተላለፍ የራዲዩ ጣቢያ ዝግጅት በተላለፈ ፕሮግራም  ለምን ያን ያህል ተረበሸ?

የግንቦት ሰባት አመራር በጋዜጠኛ አበበ በለው ንግግር ለመቃወም ና ለማውገዝ የፐረፐጋንዳ ና የስም ጥላሸት ለመቅባት ጊዜአዊ የማዘዣ ጣቢያውን ዋሽንግተን ዲሲ ኤርትራ እንባሴ  ድንኮን በመትከል ለሦስት ሳምንት በዚህ ኦፐሬሽን ላይ መጠመድ ለምን አስፈለገ ?አመራሩ  ወያኔን የማስወገድ ወታደራዊ ኦፐሬሽን ላይ ይገኛሉ ፤ ያስተባብራሉ ና ያዋጋሉ ስንል ለምንድን ነው ቁምጣ፣ ገምባሌና የካው ቦይ ኮፍያ ለብሰው ማይክራፎንና ስልክ ይዘው ኤርትራ ኤምባሴ የከተቱት? ለምን ?  ጋዜጠኛ አበበ በለው ሁላችን ከምናወረውና ከምንወያይበት በተለይም ከግንቦት ሰባት ጋር ግንኙነትና ንክኬ ካላቸውና ከነበራቸው ሰዎች   ውጭ ምን የተለየ ና የተጋነነ ጉዳይ አቀረበ? የምጣድ እያለ የእንቅቡ ተንጫጫ ስለ ሻቢያ ሲነሳ የግንቦት ሰባት ሰዎች ለምን ይበሳጫሉ? ዋይ!

እኔ ጋዜጠኛ አበበ በለውን እንደተረዳሁት በግንቦት ሰባትና በኤርትራ መንግስት ያለውን ስምምነት፣ኤርትራ አለ ስለሚባሉ ነፃ አውጭ ድርጅቶችበተለይ ስለ ትህዲንና ኦነግ( በጀረናል ከማል ግልቹ የሚመራው የኦሮሞ ነፃ አውጭ ድርጅት)በሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች በቂ መረጃ አለው አበበ በለው ይህ መረጃ እንዳለው የሻቢያ ሰወችና የግንቦት ሰባት አመራር ያውቃሉ። ጋዜጠኛ አበበ በለው ያለውን መረጃ እንደአለ ለህዝብ አቅርቦ ለውጥ ና ነፃነት ፈላጊውን የግንቦት ሰባት  የዘመን ጎደኞችንና የወዳጆችን ስሜት መንካትና ልብ መስበር አልፈለገም ። ጉዳዩን እንደሌላ ግዜ ግዜ ይፍታው ብሎ እንዳተይወው በሀገር ጥቅምና ሉአላዊነት ያለው አደጋ አሳስቦታል ። ምርጫ አድርጎ የወሰደው መረጃወችን በደረጃ በማቅረብ የግንቦት ሰባት አመራር ከአባሉትና ከህዝብ ደብቆ እየሰራ ያለውን ስህተት አርሞ አማራጭ የፓለቲካ ድርጅነቱን በሀገራችንና በህዝባችን ጥቅም ብቻ ተመስርቶ እንዲሰራ ጥሬ እያቀረበ እንደሆነ ተርድቻለሁ። ይህ መሆኑ ቀርቶ የጋዜጠኛ አበበ በለው መረጃ በጨመረ ቁጥር የግንቦት ሰባት ህልውና አደጋ ላይ ይወድቃል ይህ እንዳይሆን ደግሞ ከድርጅቱ መሪዎች በላይ ለግንቦት ሰባት መቀጠል እያሰበና እየተጨነቀ ያለው ጋዜጠኛ አበበ ነው።

ሁሉም የግንቦት ሰባት አባላት በድርጅት ፍቅር ካልታወሩ በቀር አበበ በለው በጽናት የወያኔን የዘረኛ ሥርዐት ፊት ለፊት ቁሞ በመታገልና በማታገል ያውቁታል። ጋዜጠኛ አበበ በለው ይህን ግፈኛና ዘረኛ አገዛዝ የሚሰራውን የሰብዐዊ መብት ረገጣ፤ የመብት ጥሰት፣ የህግና የፍትህ ጉድለት ፤ በተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶችናየሰብዐዊ መብት ተቆሞች የሚደርሰውን አፈናና ግድያ በማጋለጥና በመታገልበአዲስ ድምፅ ራዲዩ አዘጋጅነትና አቅራቢነት ያለመታከት ለአስራ ሰባት አመት የሰራ፣በአበበ ትግል እረፍት ያጣው ወያኔ በለለበት አስራ ሰባት ዓመት የፈረደበት ምርጥና የቁርጥ ቀን ልጅ ነው ።

የዛሪው የግንቦት አመራሮች ከወያኔና ከሻቢያ ጋር ከውጭ ተንደርድረው በመግባት ፍቅር በፍቅር እያሉ ኢትዩጵያዊ በዘሩና በማንነቱ ሲታረድና ሲገደል ቂም ያሰከራቸው የዘረኛ የወያኔ መሪዎችና ተጋዳዩች አገሪቱን የደም ጭቃ እያደረጎት በነበረ ጊዜ የዛሪ የግንቦት ሰባት መሪዎች በቤተመንግሥት ከነ መለስና ታምራት አይኔ ጋር ውስኬ ሲራጩ ወጣት አበበ በለው ይህን ግፈኛናከፋፋይ ስለመፋለም ያነጋግር እንደ ነበር ምስክር ነኝ እንግዲህ የመሰለ ኢትዩጵያዊ ነው የትናንት የመለስ ዜናዊ ጎዶች ሊዋጉትና በተቀነባበረ፤ በተደራጀናኮማንድ ፓስት (ጊዜአዊ የማዘዣ ጣቢያ) በማዘጋጀት ለሦስት ተከታታይ ሳምንት ዘመቻ የተደረገበት። ለመሆኑ ይህ ዘመቻ ዓላማውና ግቡ ምን ነበር ?

በነ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋና ነአምን ዘለቀ በበላይ አስተባባሪነት በተቀናጀናበተደራጀ መልኩ በጋዜጠኛ አበበ በለው ለሀያ አራት ሰዐት ለሦስት ሳምንት ዘመቻ የተደረገበት ዋናው ምክንያት ግንቦት ሰባት አደርጋለሁ ና አለኝ ስለሚለው ጦር ፣ ግንቦት ሰባት ከኢትዩጵያ ህዝብ ጀርባ ከሻቢያ ጋር  የፈጠረው ሽርክና ግንቦት ሰባት እሳት ራዲዮን በመጠቀም ስለ ፕረዘርዳንት ኢሳያስ የፓለቲካ ተክለ ሰውነት የኢትዩጵያ ህዝብ ልብ በሚሰብር መልኩ እየተሰራ ያለው ፕረፕጋንዳ ና ሥራ ሁሉ ግንቦት ስባት በህዝብ ፊት ለመቅረብ አላስቻለውም ። በዚህ ዙሪያ በጨረፍታ ለመጀመሪያ ጊዜ በድፍረት የፓለቲካ ትችትና ግምገማ ያደረገው አበበ በለው ነው። እርሱ ያነሳው ትችት ግንቦት ሰባት የማይሸከመውና የማይመልሰው ጉዳይ መሆኑን አመራሩ ያውቃል ስለዚህ ይህ አበበ በለው ያነሳው ትችት ወደ ህዝብ ወርዶ መነጋገር ሳያመጣ የግንቦት ሰባት አመራር የወሰደው እርምጃ አበበ በለውን ማፈንና ቢችሉ አንገት በማሰበር ሁለተኛ በዚህና በዚህ ጉዳይ እንዳይተነፍስ ማድረግና ሌሎች ጋዜጠኞች፣የሲቢክ ማህበር መሪዎች ፤ አክትቢስቶች፣የድህረ-ገጽ አዘጋጆች፤ የፓል-ቶክ ባለቤቶች ናመሪዎች፤የፓለቲካ ተንታዮችና ፀፊዎች፣የሻቢያና የኢሳያስን አደጋ የሚውቁ ነባር የኢትዩጵያ ሠራዊት አባላትና የሚሊተሪ ጠበብቶች፣እውቅና ተመክሮ ያላቸው የዲፕሎማሲ ና የፓለቲካ ሰወች፣በሻቢና በኤሳያስ አፈዎርቂ አምባገነን ሥርአትና በወያኔ ዘረኛ ሥርዐት ሰለባ የሆኑ ኢትዩጵያውያንና ኤርትራውያን ሁሉ እንዳይነጋገሩ፣ እንዳይወያዩ በግንቦት ሰባትና በሻቢያ ካድሪዎች በተነቀባበረና በተደራጀ ደረጃ ዘመቻ በአበበ በለው ዘመቻ ተጀመረ ። ዘመቻው አበበ ባነሳቸው ጉዳዩች መልስ በመስጠትና በማሳመን ሳይሆን አበበን ዝቅ ሊደርግና አንገት አስደፍቶ ዝም እናሰኘዋለን የሚለውን አካሄድና ዘለፋ በመጠቀም ከዋናው ማዘዣ ጣቢያ በነ ነአምፕን ዘለቀና ብርሀኑ ነጋ በሚሰጥ የፕሮፓጋንዳ ና የዘለፋ ዝግጅት በባል-ቶክ ተኩስ ሲደርጉ ከርመዋል። በዚህ በኩል እንዲተባበሮአቸው የፓል ቶክ ርሞችን ፣ገጣሜዎችን፣የድህረ ገጹ አዘጋጆችን፣ ጸሐፊዎችንና የፓለቲካ ተንታዮችን ትብብር ጠይቀው ነበር ።ግንቦት ሰባት የነደፈውን ሁለ ገብ ትግል በአበበ በለው ላይ ተግባራዊ ለማድረገብ ዘመቻ አድርጎል ሌላው ቀርቶ የወያኔ ሜድያ አበበ በለውን ለማጥላላት የሰራውን አኬልዳማ ግንቦት ሰባት ለአሁኑ የማጥላላት ዘመቻ እንዳለ ካሴቱን እንደ ማስረጃ ተጠቅመውበታል በዚህም የድርጅቱን አናሳነትና አቅመ ቢስነት አሳይተዋል እነ ግንቦት ሰባት ይህን የተቀነባበረ ዘመቻ ያደረጉበት ዋናው ግቡ አበበ በለው በእነርሱ ውጊያ ተደናግጦ በሰራው ሥራ ተፀፅቶ በነ ነአመን ዘለቀና ብርሀኑ ነጋ ታጅቦ በእሳት ቴሌብጅን ቀርቦ ሲናዘዝና ከዚህ በኃላ ስለ ሻቢያ፤ ኢሳያስ አፈወርቂና ግንቦት ሰባት የሚወራና የሚተች ቢኖር ይህን እናደርጋለን አይነት  የዘመቻ ቅንብር ነበር።ለዚህ ነው ግንቦት ሰባት እራሱን እንደ መንግስት ስለሚቆጥር። ርእሴን ስደተኛው አምባገነን መንግሥት ስል የሰየምኩት። አበበ ያነሳው ርእስ የሺዎች ርእስ ነው አበበ ላደረገው ሥራና ለሚደረገው አስተዋፅኦ ህዝቡ ይወደዋል፣ ያፈቅረዋል።አበበ ሲሳሳት ለመታረም ዝግጅ የሆነ ግልፅና በሳል መሆኑን ጎደኞቹ ይመሰክራሉ። አበበ በለው በሦስት ግንባር የተከፈተበትን ጦርነት በሀሳብ አሸናፊነት አሸንፎአል

በመጨረሻ እውነቱንንሀቁን እያወካቹሁ ዘረኛው የወያኔ መንግሥት ከሚደርገው አፈናና ግድያ ወጠን በዚህ በነፃነት በምንኖርበት ሀገር ለሀገራችንና ለህዝባችን የተሻለ እናደርጋለን ስንል ሀሳባችንን በሀሳብ ማሸነፍ ሲችሉ በተቀነባበረና በተደራጀ መልኩ መብትና ነፃነታችንየሚጋፈፍን ልንታገላቸው ይገባል። በኢትዩጵያ ፓለቲካ በተለያየ ደረጃ በቀደምነት አስተዋፅኦ ና እሽራ ያላችሁ እንዲህ ዓይነት ፀያፍና አስነዋሪ  አካሄድ ማስቆም አለባችሁ።

አምባገነን መሪዎች የሚፈጠርቱ አምባገነን አስተሳሰብ ካላቸው ሰወች ነው። እኛ ካልነው ውጭ ሊላው ሀሳብና ሀሳቡን ያመነጨው መጥፋት አለባቸው ከሚሉ ሰዎች ነው የሚወለደው። አምባገነኖችን የምንወልደው እኛው ነን ።

ኢትዩጵያ ለዘላለም ትኑር፡፡፡፡፡